# ያሻዋል ተተኪ

መታወቅን ናቀ... ከእውቀት ተዋዶ
መኩራራትን ጠላ... ከዲኑ ተዋዶ
በቀን በመዓልቱ... አንገቱን የደፋ
የጥበብን ብርሃን... በስውር ያሰፋ።

አንደበቱ  ልቦናው... ከቁርዓን ወግኖ
ነፍስያውን ቀጣት... በተቅዋው አመንምኖ
የስኬቱ ስምረት... አልቀረም ታፍኖ
አገር ዲኑን ሁላ... በገሃድ ከሽኖ
ዘኪን አሳወቀ... በዓለም ተበትኖ።

ሱብሃነሏህ!...ኢንሻአሏህ!
እናት ትውለድ መንታ... የመሰለ ዘኪ
ቫይረስ ጀርሙን... በጥበብ አዋኪ!
የትም ይሁን መቼ!... የሰናይ ሰባኪ
ልብ ያለው ልብ ይበል!... ያሻዋለ ተተኪ።

ያ! አኹና ዘኪ
ዶክተር ዘኪ ሆይ!

ፋና ይዘህ ቁመህ...ፋና ስታበራ
ማይም ጠማማውን... በውቀት ስታገራ
የዱንያ ግዝፈት... ካንተ ተቆራርጦ
የችሎታ ብዛት... በአንተ ተቀምጦ
ተራራውን ቧጠህ... ከጫፍ ስትወጣ
የአሏህ ምሳሌ ነው... የማስጠንቀቅ እጣ!

ያሳትር!... ያረብ!

ይብላኝነት... ለርሱ... ላስተባበለ
በዱንያ ጠዓም!... ሰክሮ ለዋለለ
ሐቅ ሲነገረው... ፊቱ ለ-ሚገረጣ

## ከማወቅ ከመማር ለሆነ ባላንጣ!

ሀያ!... ሀያ!... አሻም... አሻም...
አዋጅ... አዋጅ!... እንውጣ ደረጃ
ከደረጃው በስቲያ... አለ ትልቅ ግምጃ
አቁሙ በአንድዬ... አንጃና-ግራንጃ
ደረጃውን መውጣት... ያስገኛል ደረጃ
መጠየቅ አይቀርም... ያስቀጣል እኔ-እንጃ!

አዋጅ!... አዋጅ!...

እድል... እጣችሁን ከምትራገሙ
የዘኪን አይታችሁ ከምትገረሙ
ተስፋ-ማስቆረጥን- ከምታጣጥሙ
ያቅማችሁን--ያህል... ውጡና ቅሰሙ
ከመቃብር በፊት... ስሙ የማትሰሙ::

ኑ!... እንቅመሰው የእውቀትን አሞሌ
እንጠቃቀመው የዘኪን ምሳሌ
ፅልመትን ለማብራት አግኝተናል ወኔ
ሁሌም ማመካኘት ያስገባል... ኩነኔ
ማይምነት አይደለም !

## በአንድ ሌሊት፤ ሁለት ሽልማት

መታወቅ፣ ዝና ለርሱ ደንታም አልሰጠውም:: የዚህ ኢትዮጵያዊ ውሎ ለሰው ልጆች የድንቁርና ደዌ-ቤዛ በመሆኑ ዛሬ የርሱን የህይወት ውጣ ውረድ በጥቂቱ ንቃኛለን!

ዘኪ አብዱላሂ ሸሪፍ ይባላል በእውቀት ወርቀ-ዘቦ ላይ የምጥቀትን ቆብ የደፋ ዶክተር ነው:: ባደረገው ፀረ ደዌ፣ ፀረ ማይምነት ተጋድሎ በሌሎች የርሱ ባልንጀሮች-መጢቆች ተመርጦ የክብርና የኃላፊነት ሊሻኑን ተቆናፅፏታል::

አላህ (ሱ.ወ) ሁሌም ፍትሃዊ የሆነ ጌታ ነው የሰው ልጅ ሁለንተናን በላቀ ጥበቡ ሲያምነሸንሸው ከፍትወት ጠብታነት ባሻገር የረጋ ደም አርጎ፣ አጥንት ስጋን ቸሮ ሰው ... እንካ... ይመስራች አለምን ሲል... ዱንያ በመምጣቱ የተከፋ ይመስል ሁሌም ህፃን ለብስራቱ ደወል- ያለቅሳል... ዘኪም አንዱ ነበር!

ህፃናቶች በህፃንነታቸው መሳ-ለመሳ ቢሆኑም፣ የሚኖረበት አካባቢ፣ የወላጆች ሁናቴ፣ የማህበረሰቡ ብቃትና ጥራት ብሩህ ተስፋቸውን ለየቅል አድርጎ ይኮተኩታቸዋል። እንግዲህ! እያንዳንዱ ለእያንዳንዱ እያንዳንዱ በእያንዳንዱ የተቀዳጀው መረዳት፣ የመማማር ሰብዓዊ መብት በስስት ካልመነመነ በስተቀር በለት-ተለት ህይወታችን ውስጥ ደንዳና ኃላፊነት ነው። የዚህን የኃላፊነት ሚና ለሰፊው ሕዝብ ለመጫወትና ሁሌ ችግር፣ ሰቆቃ፣ የፖለቲካ ጭቅጭቅን ለሚሰሙ ወገኖች የዚህ ኢትዮጵያዊ ገድልን ሲሰሙ ብሩህ ተስፋ በምናባቸው ይሰርፅ ዘንድ ብሎም በመማሩ ስንክሳር ውስጥ ገብተው የስደቱ ሸክም እያንገዳገዳቸው ያንን የእውቀት ተራራ ለመውጣት ሊሚጣጣሩ ወገኖች አሻም!... ለማለት ነው ዛሬ ዘኪን በብስራትነት ይዘን ብቅ ያልነው።

ዶክተር ዘኪ የካንሰር መንስኤን ለማመላከት ሁለት የካንሰር ጂኖችን በምርምር አግኝቶ በራሱ ስም ZS (ዘኪ ሸሪፍ) ብሎ ለመላው የዓለም ህብረተሰብ እንካችሁ ብሎ ኢትዮጵያዊ አልበርት አንስታይንነቱን አሳውቋል። ይህ ሳይንቲስት በመላው ዓለም የእውቀት ደርሳን ውስጥ ስሙን ያስከተበ፣ ብሎም በዋሽንግተን ዲሲ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከሚገኙት እውቅ ዶክተሮች መሃል ተመርጦ የ2004 Hall of Fame Award (የዝና ማዕከል ሽልማትን) በ April 18 የተቀበለ ውድ ያገር ልጅ ነው! ዘኪ ሸሪፍ! ትንግርቱ አሁንም ይቀጥላል... በዚያኑ ሌሊት ከብዙሺ ሳይንቲስቶች፣ ዶክተሮች መሃል ተመርጦ በ Oregon በሚገኘው International Union of Cancer Researchers በሌለበት ሌላ ሽልማት ተሸልሟል! ለዚያ ነበር በአንድ ሌሊት ሁለት ሽልማት ብለን የጀመርነው።

አዲስ አበባ የተወለደው ዘኪ የልጅነት አዕምሮውን የከፈተው በቁርዓን ብሎም የአንደኛ ደረጃ ትምርቱን በአባድርና በዘነበወርቅ ትምህርት ቤት ነው የተማረው። Double በመባል በሚታወቀው የክፍል ማዘለል ዘዴ-ተጠቃሚ ነበር ዘኪ! በቃ በdouble በፍጥነት የልጅነት ትምህርቱን እያገባደደ፤ 9ኛ ሲደርሰ ሁሉንም ትምህርት በመጽፈኑ (A በማምጣቱ) አንደኛ በመውጣቱ ሽልማቱን ያኔ ነበር የጀመረው። ወደ አስረኛ በገባ ሁለት ሳምንት ለእድገት በህብረት ዘመቻ ተጠርቶ ወሎ ውስጥ ውርጌሳ የምትባል ከተማ ይዘምታል ከሚወደው ትምህርትም ይቆራረጣል፤ አባቱ ግን አልጨከኑበትም እዚያው ትንሸዬ ከተማ ውስጥ እያለ በመላላክ (Correspondence) በለንደን በኩል ይቀጥላል የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ባለፈ በሶስት ወር በሙሉ Scholar Ship አስር አስራ አንድ አስራ ሁለተኛን ሳይማር University of Alabama ሲገባ በጣም ልጅ ነበር ትምህርቱንም ቀላል ሆኖ አገኘው የአንድ ዓመት ኮርስን በጥረቱ በማስወገድ ሌላ ዳግማዊ Scholar Ship

ተቀዳጀ ወደ University of Wisconsin… ዲግሪውን በሁለት ዓመት አገኘ:: ከአንድ ዓመት በኋላም ማስተርስ ዲግሪውን ደገመ::

PHD ውን ለመሥራት ወደ Houston Rice University ገብቶ እየተከታተለ ሳለ Howard University ለሁለት ተማሪዎች ብቻ የሰጠውን ዕድል ዘኪ በጁ ያደርገውና በፍጥነት እንዲመጣ ያደርጉታል ከ Johns Hopkins University ጋር በመተባበር ጥናቱን በመካሄድ የዶክትሬት ዲግሪውን በሶስት ዓመት ይጨርሳል::

የተባበሩት መንግሥታት አገርን እንዲያገለግል ባደረገለት ጥሪም ተምሮ ለማስተማር ኢትዮጵያ ይገባና በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ዶክተሮችን ማሰልጠን ይጀምራል ተማሪዎቹ ለተባበሩት መንግሥታት ባደጉት ግፊት ተጨማሪ ሶስት ወር ያሰለጥናቸዋል:: ዳግም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተጠርቶ ኒዮርክ በመምጣት ለደቡብ ምስራቅ አሲያ የህክምና ተቋማት ስርዓተ-ትምህርት ሲያቀናብር አለምን ሲቃኝ፤ ቅር የተሰኙት አስተማሪዎቹ የዲኘሎማቲክ ሥራውን እንዲተውና የተማረውን ለሌሎች እንዲያስተምር ሲገስፁት ስም ዝናውን ትቶ ቃላቸውን በመስማት ወደ ትምህርቱ ዓለም ይመለሳል:: ካሊፎርኒያ በሚገኘው Stanford University በመምጣት የሁለት ዓመት ጥናት በማካሄድ በ Molecular Medicine የምስክር ወረቀቱን በማግኘት እዚሁ በሚገኘው George Town University በመምጣት የማስተማር-የምርምር የሳይንቲስትነት ተግባሩን ተያይዞታል::

በዚህ እሰየው በሚያሰበለው ጥናቱና ብቃቱ ታጭቶ ነበር ጣምራ ሽልማቶችን በአንድ ሌሊት የተቀዳጀው ግና! ሲሸለም ቀረርቶ አላሰማም ረጋ ሰከን ብሎ ፊቱን በፈገግታ እያንበሸበሸ ልብ የሚማርክ ትህትናን እያከለ የሶስት ደቂቃ ንግግርን ለማድረግ ወደ ወርቃማው ማይክራፎን በዝግታ ጠጋ አለና ወረቀቱን ከውስጥ ኪሱ አወጣ… በፍፁም በጭራሽ!… ኩራት አይታይበትም… ለምን?… የሚል ካለ

"ኩራት የችሎታ ማነስ ነፀብራቅ ነው"

"ኩራት የጎደለን ለመሙላት የሚደረግ የውር ድንብር አካላዊ መወራጨት ነው"

"ኩራት የጥራዝ-ነጠቆች ኩታ ነው"

"ኩራት እኔ አውቃለሁ! እኔ በልጣለሁ በማለት የሚከናወን የድንፋታ መማፀን ነው:: "

"ያላዋቂ ምልክቱ… መኩራቱ"

"ያላዋቂ ምልክቱ እዩልኝ ስሙልኝ ማለቱ"

ግና ዘኪ አንገቱን የደፋ ትሁት ነው እግሮቹን አጣጥፎ አንገቱን ደፍቶ በሀይማኖት አባታችን (ሙፊቲ ሙሃመድ ሲራጅ) ጥላ ሥር ተቀምጦ ሲማር ሲያስተምር ሆድን

ያባባል... እነሆ! ሽልማቱን ሲያነብ የተናገረው ንግግር አንኳር! አንኳሩ እንዲህ ይደመጣል-ሲጀምር...

"ቢስሚ አሏህ-አርህማን አረሂም በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ መሃሪ በሆነው ብሎ አጻራሹን ፀጥ-ረጭ አደረገው።

## በአንድ ሌሊት፣ ሁለት ሽልማት

ከባለፈው የቀጠለ

ዘኪ

የሰናይ ምግባርን ፋና ይዞ፣ የሰው ልጅን ከበሽታ በመፈወስ ሰላም፣ ጤና ሊሰጥ ነው ታጥቶ የተነሳው የምርምር አድማሱንም አስፍቶ ሌት-ተቀን ጥሮ-ግሮ ለበሽታዎች መፍትሔ ለማግኘት የተነሳው። ከደም-ከስጋው የተዋሃደው ሀይማኖቱም እንዲህ ብሎ በራስ መተማመኑን አጎልብቶለታል፣ ለበሽታዎችም መጽሃኒት እንዳለ ገልጾለታል።

"በታመምኩም ግዜ እርሱ ያሽረኛል"

አል-ሹዓራ- ቁጥር 80

ከኢስላማዊ ምንጻው ኩርማኑን (Slice) አግኝቷል። ለዚህ ኢትዮጵያዊ አልበርት አንስታይን ያንሰዋል "አንድ ቀን አምላክ ሲለው" ይላል በንግግሩ ላይ አንድ ቀን የምርምሩ ትሩፋት ለሰው ልጆች ፍቱን መድሃኒት ሲያስገኝ... እናት አገሩን፣ ሀይማኖቱን፣ ጥቁር ሕዝቦችን አሳውቆ "የኖቤልን ሽልማት ይጎናጸፈው ይሆናል... ለንጉስ ፈይሰል ሽልማትም ይጠራ ይሆናል... ኢንሻ አላህ! ያ ለጋ ወጣት እያለ የእውቀት ፍኖት ወደ ተቀየሰበት ቀዬ ከአገሩ ከኢትዮጵያ የተሰደደው ዘኪ!... የዛሬው ዶክተር ዘኪ... የዛሬው ፕሮፌሰር ዘኪ የዛሬው ሳይንቲስቱ ዘኪ! ትሁቱ ዘኪ! አንገት ደፊው ዘኪ! ሙፈቲህ ሙሃመድ ሲራጅ የሚወዱት... የሚመርቁት ዘኪ!... አዎ በፍፁም በርሱ እድሜ የማይገኘውን ጣምራ ሽልማት በአንድ ሌሊት የተቀዳጀው። የሁለት የካንሰር ጂኖች ባለቤት በስሙ ZS ዘኪ ሽሪፍ ብሎ የሰየማቸው በርግጥ ምንጻው የትዬ-ለሌ ነው እርሱ አምላክ ነው የሚያውቀው በቃሉም እንዲህ ብሏል

(ነፍስን) ህያው ያደረጋት ሰው ሰዎችን ሁሉ ህያው እንዳደረጋት ነው

አል-ማኢዳህ - ቁጥር 32

አሁን የምናቀርበላችሁ ሽልማቱን ሲቀበል ያደረገውን ንግግር ነው የንግግሩን የእንግሊዝኛ ኮፒ በኢንተርኔት ከ Ethiopian Muslims.com ማግኘት ትችላላችሁ።

ይህን የምስራች ላልሰሙ አሰሙ ድርቅ፣ ረሃብ፣ ኤድስ ወይም 'ሩጫ' ብቻ አይደለም መታወቂያችን ዘኪን መሰል ሳይንቲስቶች አሉን እንካችሁ ያንን ያማረ

የተዋጣለት ዲስኩር ሲስሚላህ አርህማን አረሒም (በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው) ሲል አዳራሹ ፀጥ-ረጭ አለ...

የዝና- ማዕከል ዲስኩር

**April 18/2004**

1. የኔ በዛሬው ምሽት ከናንተ ጋር እዚህ መገኘቴ አጋጣሚ ወይም ያልታሰበ አይደለም ግና የአምላክ ፈቃድ ነው ብዬ አምናለሁ:: አምላክ ወስኖ ያዘዘውን እርሱው አዕድቆ ቀጣይ ያደርገዋል::
2. እውነትን መፈለጉ ለኔ ግላዊና የሙያ ተግባሬ ነው:: ሳይንስ የአለማትን ሁናቴ እጥንቶ-ለመተንተን-ለመቃኘት የሚረዳ ግሩም መሣሪያ ነው:: አለማት በአያሌ ምስጢራዊ ፀጋ የተሞሉ ናቸው:: ከተፈጥሮ ፀጋዎች አንዱ ህክምና ነው! በህክምናም ዘርፍ በመሆኔ ማንኛውም በሰው ልጆች ዘንድ ለታወቀ በሽታ፣ አምላክ መድኅኒት ጭምር መፍጠሩ ዕሑ እምነቴ ነው::
3. ለዚያም ነው እኔ በጥናት ምርምር አፀድ ውስጥ የገባሁት:: ዘርፉም Cancer (ነቀርሳ) ሲሆን ንዑስ ምድቤም 'ሞለኩላር ሜዲስን' ይባላል::... እውቀትን መሻት ዘላለማዊ አላማና ግብ ነው::
4. እውቀት አደራ ነው:: የሰው ልጅ ደግሞ የዚህ አደራ አገልጋይ ነው እንደ አገልጋይነቱም ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ይሸከማል::
5. ዛሬ፣ ታላቁ አሳቢ ባትሆኑም... ግን አስቡ
   ታላቁ ሳይንቲስት ባትሆኑም... ትሆኑ ዘንድ የጋለ ፍላጎት ይኑራችሁ
   ታላቁ አስተማሪ ባትሆኑም... ትሆኑ ዘንድ ፍላጎቱ ይኑራችሁ
   በጣም የተሳካለት ሰው ባትሆኑም... በማንኛውም መልኩ ስኬትን ተጎናፀፉ::
6. ለሰፊው ሕዝብ ግልጋሎት መስጠት፣ ክብርና ግዴታ ነው:: ክብር የሆነበት ምክንያት መሰረታዊ ህብረተሰባዊ አንደበትን በአምድነት ያበጃልና!... ጥበብ ሙያ እውቀት ምንጫቸው ከፈጣሪ ሲሆን እጅ-ለጅ ሆነው ባንድ ይጓዛሉም:: ፈጣሪን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ መሆኑ ተነግሯል:: ባንፃሩም ጌታን መውደድ የእውቀት መጀመሪያ ነው:: ከትውልድ አገሬ ኢትዮጵያ ገና ለጋ ወጣት ሳለሁ ነው የተሰደድኩት ሙስሊም እንደመሆኔ መጠን የትም ይሁን መቼ እውቀትን እንድፈልግ ታዝዣለሁ::
7. ለታላቁ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የኔ ማንኛውም አስተዋፅኦ በሕዝብ ዘንድ ከተወሳ ምክንያት ይኖረዋል:: ምክንያቱም:- ቀጣዩን ለሰው ልጆች ዋጋ ያለውን እውቀታዊ ቅኘት ለማጎልበት ነው:: በዛሬው ምሽት ዋሽንግተን ዲሲ የልጇን ሕዝባዊ አዕድቅኦ እንደ በዓል የምታከብር ከሆነ ለየትኛው ልጅ ወይም ልጃገረድ

አርዓያ እንደምሆን ባላውቀውም በጋለ-ፍላጎት የበለጠ ጠንክሬ እሰራለሁ፡ ህልውናችን የቁስ ፍሬ-ነገርን የተቸረ ነው ከዚህ ጊዜያዊ ዓለም በመነጩ የቁስ ፀጋዎች ዛሬ እዚህ በመገኘቴ ቅንጣት ታህል እንኳ ያንን የሚሞላ ከሆነ "ጥራት-ልዕልና ለጌታ ይገባው" ማለት አለብኝ፡፡

8. ለወጣቶች ማበረታቻ የሚሆኑ ታላቅ፡- በምክንየታዊነት ተመኙ፣ በሙሉ ልብ ተመኙ፣ በጋለ-ፍላጎት ተመኙ ማንም ከምኞቻችሁ እንዳያቅባችሁ! ሁሌም አስታውሱ እውቀት ክብደት የለሽና ቁልፍ አልባ ናት፡፡ ዘወትር ከራሳችሁ ጋር ልትሸከሟት የምትችሏት ፀጋ ናትና!
   - በእርግጥ ለዓመታት የገነባችሁት... በአንድ ሌሊት ሊፈርስ ይችላል... ቢሆንም ግን ገንቡት፡፡
   - ለጠንካራው ሥራ ተግባራችሁ ላትመሰገኑ ትችላላችሁ ...ግን በማንኛውም መልኩ ጠንክራችሁ ሥሩ
   - ካካበታችሁት ላይ ምርጡን ለዓለም ትሰጡ ይሆናል፡፡ ...ግን በማንኛውም መልኩ ተመኙ
   - ዛሬ መልካም ያደረጋችሁትን... ነገ ሰዎች ሊረሱት ይችላሉ... ግን በማንኛውም መልኩ መልካምን አድርጉ

     ታያላችሁም በመጨረሻ የትንታኔውን እውነታ ቁም ነገሩ ነበር በናንተና በጌታ በፍፁም አልነበረም በናንተና በነሱ የነገሩ ሁኔታ

9. ማንኛውም ጥረት ያለ ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድ አጋርነት ከፍፃሜ አይደርስም በመጀመሪያ ወላጆቼን ቀጥዬም ዘመድ ጓደኞቼን ላልተቋረጠው እርዳታቸው ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በተለይም እዚህ ላሉት የፈርስት ሒጅራ ማዕከል ቤተሰቦቼ እኔን ለዚህ ሽልማት ላጩኝና ለመረጡኝ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ለ Hall of Fame አካላት ይህን እውቅና ስለሰጡኝ አመሰግናለሁ፡፡ በ Eugene Oregon የሚገኘውን የነቀርሳ ተመራማሪዎች ህብረት በሌለሁበት ሽልማት ስላዘጋጁልን አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ባጋጣሚ የነርሱን ሽልማት ሔጄ መቀበል አልቻልኩም ስለምን? በቀላሉ እኔ እዚህ ነኝ - ዋሽንግተን ዲሲ አሸንፋ አስቀርታኛለች፡፡

10. በዛሬው እለት ለቅርስ-ሽልማት ተሰባስበናል፣ እምብዛም ለናንተ የምተወው ቅርስ ላይኖረኝ ይችላል ግና በነዚህ አበረታች ታላቶች እሰናበታችኋለሁ
    ማድረግ እንደምትችሉ እመኑ... ታደርጉታላችሁና ሁሌም እምነትን ተጠቀሙ... ጠላታችሁ ፍራቻን ሊጠቀም ሊያደባ ከተራራው ጫፍ ላይ ትወጣላችሁ አምላክ ሲለው አንድ ቀን

በጣም አመሰግናለሁ

ዘኪ ሽሪፍ

አድማጮቻች የዚህ ተከታታይ ዘገባ ቅንብር ያለ ወንድም ኑሩ ይማም የቪዲዮና የፅሁፍ ማስረጃ እሙን ባልሆን ነበር፡፡ ወንድም ኑሩ ይማምን በመላው ታዳሚያችንና በዝግጅት ክፍላችን ስም የላቀ ምስጋናችንን ልናቀርብለት እንወዳለን፡፡

# የተምር ሚስጥር

ይህ! ያበቅ-የለሽ ትንግርታዊ ምሪት የሚበሰርበት፣ ግነት የሌለበት፣ ራስ ወዳድነት ድርሽ ያላለበት፣ ሳይንስና ቁጥርዓን የሚነፃፀርበት፣ ለፍትሃዊ ችሎት ለአዕምሮ የሚቀርበት፣ የቁርዓንና የሳይንስ ክፍለ ጊዜ ነው::

" ዛሬስ ምን አለ? ከተባለ... ምን ጠፍቶ እውነት ሞልቶ፣ ከአፅናፍ - አፅናፍ ናኝቶ፣ አንደ ማለዳ ፀሀይ በርቶ!:: አንዱን ለዛሬ ጀባ ከሙዳው ልብ ከገባ! ቅጠሉ እንደ-ዘንባባ፣ ጣዕሙ የሚያባባ ገላ-ሰውነትን የሚገነባ:: የተምርን ምስጢር እንስማ ሳይንሱ ከቁርዓን እንዲስማማ::

ዛዲያ ድሮ-ድሮ በአገራችን 'ተምር' ሲባል የሙስሊም ብቻ ተደርጎ ተሰይሞ ሰፊው ሕዝብ ከጣዕምና ከቤዛነቱ እምብዛም አለመቀራረቡ ለምን ይሆን? ዛሬ ደግሞ የ Diet (የተመጣጠኘ ምግብ) መስፈርትን አሟልቶ በአሜሪካ ሱፐር ማርኬቶች በብዛት መገኘቱስ ለምን ይሆን?

እንግዲህ በነብያዊ ፈለግ ተጉዘን ሳይንሳዊ ይዘቱን ለመጠቋቆም እንሞክራለን:: በነብዩ ሙሃመድ (ሱና) መሠረት ህፃናት ሲወለዱ ምርጥ የሆነ ተምር ይደቅና በአፋቸው ውስጥ ይላወሳል:: ድርጊቱ ለአያሌ ዘመናት እየተከናወነ ያለ ቢሆንም የእንግሊዝ ተመራማሪዎች ሳይንሳዊ ይዘቱን ከማብሰራቸው በፊት ከሙስሊሞች በቀር እንብዛም ልብ ያለው አልነበረም! ታዲያ ለሰው ልጆች ፊውስ ተልከሃል የተባሉት ነብዩ ሙሃመድ (ሰ.0.ወ) ለምን ተግባሩን አስተማሩን?

በ British Medical Journal ቁጥር 6993 በ June 10, 1995 እትሙ "አዲስ ለተወለዱ ህፃናት መርፌ ሲወጉ ወይም ሲገረዙ ህመማቸውንና ልቅሶአቸውን ለመቀነስ በተደረገው ጥረት በ60 ህፃናት ላይ ምርምር ይደረግና አመርቂ ውጤት ተገኝቷል:: ከፈሳሽ ጋር ጣፋጭ ታክሎ የሚሰጣቸው ህፃናት በመርፌና በግርዛት ወቅት ልቅሳአቸውና የልብ ትርታቸው መቀነሱ ተረጋግጧል::

ከላይ የተዘገበውን የእንግሊዞች ምርምር በነብያዊ መረጃ እናንፀው ዘንድ ከቡኻሪና ከሙስሊም የነብያዊ ምሪት ጥርቅም አንድ እጥር ምጥን ያለ ሐዲስ እነሆ!

አቡ ቡረይዳ ከአቡ ሙሳ የዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ይነበባል "አዲስ የተወለደ ህፃን ነበረኝ ወደ ነብዩ ሙሃመድ (ሰ.0.ወ) ወሰድኩት ኢብራሒም ብለው ስም አወጡለት በመጠቀልም ተምር አኝከው በአፉ ውስጥ ለወሱለት"

ብዙ ነብየዊ ትምህርቶችን ማቅረብ ቢቻልም ቅሉ ልብ ያለው ልብ ካለ ይኸው ይበቃል::

ተምር ከ70-80% የሚሆን ስኳር አለው Fructose እና Glucose የሚባሉትንም ጣፋጮች በጥምረት ይይዛል:: ከሰውነት ውስጥ ለሚከናወነው የምግብ መፍጨትና

መሰራጨት (digestion) በጣም ቀላል ነው አዕምሮንም ይረዳል። ተምር 2.2% protein አለው ከቫይታሚኖችም B1 እና B2 ይይዛል። ለሰውነታችንም ከሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮች potassium, sodium, calcium iron, copper እና manganese አለው።

በተምር ውስጥ የሚገኘው potassium የወሊድና የግርዛት ደምን ለመቀነስ አስተዋፅኦ እንዳለው ተደርሶበታል። ይህንን ሁናቴ በቁርዓን ጥላ ሥር ስነቃኘው አላህ የማርየምን ወሊድ ያቀልላት ዘንድ የእየሱስ ተዓምራዊ ውልደት ይሰምር ዘንድ እንዲህ ብሏት ነበር።

የዘንባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዛት ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና።

መርየም - 25

ይቀጥላል እውነቱ፣ ፈጣሪ ነው መሠረቱ፣ አቤት ደስ ማለቱ እውነትና ንጋት አብሮ መጥራቱ፣ ከአዕናፍ - አዕናፍ መብራቱ፣ ታዲያ ለምን ነው ልብ አለማቱ? ይኸው ከቁርዓን ምልክቱ በማስተባበል ለሚሰነብቱ። እነርሱም (ቁርዓን) ለነሱ እውነት መሆኑ እስኪገለፅላቸው ድረስ በአዕናፍቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶች በእርግጥ እናሳያቸዋለን ጌታህም እርሱ በነገሩ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን? ንቁ እነርሱ ከጌታቸው መገናኘት በመጠራጠር ውስጥ ናቸው-ንቁ እርሱ ከነገሩ ሁሉ አውቀቱ ከላይ

## የሥነ ፍጥረታት ሳይንሳዊ ግኝት፤ በቁርዓን ሲካተት

መቼም ጆሮ አይሰማው የለ! የአላህ የተዓምር ግዝፈት የሙያ የብቃቱ ምጥቀት ለየቅል ነው ባንፃሩ የቁርዓን ሳይንሳዊ ድምቀት ዘመን ግዜ የማይሽረውን የህይወትን የፍጡራንን ምስጢራዊ ገፅታ ሰንቆ የሰው ልጅ ለእውነታ ሲራብ የመንፈስ ጻቦ ሆኖ ፍጃታውን ይሞላል።

እንግዲህ መሬት ሰማይ ክዋክብት ሁላ ኘላኔቶች ሁላ በአንድ ላይ የተጣበቁ ነበሩ አንድ አካል ነበሩ ብንላችሁ 'በሬ ወለደ' የሚለው የክርክር ጋሻ ብቅ ይል ይሆናል - ቁርዓን ነው ያለው ብነል የምዕምናን ልብ በደስታ በመደለቅ እውነቱን ሊሽምት ይዘጋጅ ይሆናል ወዲያውኑ አስተባባዮች ቅፅበታዊ ምክንያታቸውን በምናብ ይስሉ ይሆናል! በድንገት ሳይንስ አረጋግጦታል ስንል እውነት መራራ በመሆኑ እየመረራቸው ያጻምጣሉ።

ዛሬ የምንነጋገረው ስለ Big Bang ነው (ስለታላቁ ፍንዳታ) በስነፈለክ ተመራማሪዎች ሲብራራ ስነ-ፍጥረታት አንድ ትልቅ አካል ነበሩ ከዚያ Big Bang ታላቅ መለያ (ፍንዳታ) ተከሰተ ይህም የክዋክብት ጥርቅምን (Galaxy) ፈጠረ ከዚያም ክዋክብት ተገኙ በመቀጠል መሬትን መሣይ ኘላኔቶች፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ ወዘተ ተከሰቱ የሥነ ፍጥረታት ምንጭ ድንቅና ልዩ በመሆኑ ባጋጣሚ የመገኘታቸው ጉዳይ ሳይታለም የተፈታ ነው። ይህንንም የ Big Bang አውነታ ነበር ቁርዓን ከ1400 ዓመታት በፊት ጥርት ባለ መልኩ ያስቀመጠው።

እነዚያ የካዱት ሰማያትና ምድርን የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መሆናቸውን አያውቁምን?

አል -አንቢያ - 30

እንግዲ በዚህ ጭው ባለ በረሃ ላይ የአቧራ ጨለማ በቀን በሚነግስበት ምድር ላይ የነበረው አሸዋና ድንጋይ እንደ እሳት በሚፋጅበት መካ በዚያ ድንቁርና ድቅድቅ ያለ ፅልመቱን በነሱ ላይ ባነገሰበት አረቢያ ከ1400 ዓመት በፊት ማን ነው ይህንን ሳይንሳዊ ሐቅ ተፈላስፎ ለመጭው ትውልድ ያሰፈረው።

እኮ ማን ነው? የትኛ ቤተ-ምርምር (laboratory) ነው ያጠናው? የትኛው ተሞክሮ (Experiment) ያረጋገጠው የትኞቹ ዶክተር ኘሮፌሰር ሳይንቲስቶች ተመራምረው ያፀደቁት እያንዳንዱ ከግላዊ ግትርነት በመራቅ እራሱን ሊጠይቅ ይችላል ምላሹም የራስ ጻሽን ተራራ ቧጦ የመውጣት ያህል አይርቅም ቀላል ነው - ልብ ያለው ልብ ካለ።

ይህ ነው አለማዊና መንፈሳዊ እሴትን ያጣቀሰ እውነታ በምርምር በጥናት በምክንያታዊነት በዘላለማዊ የእምነት ትጋት የተገነባ መሠረት ነው ቁርዓን። በባለፈው ሳምንታት መጣጥፎችን ላይ የሊቁ አልበርት አንስታይን ሀረግ አብስረናል ዛሬም እንድገመው "ሳይንስ ያለ ሀይማኖት መሠረት አልባነው ሀይማኖት ያለሳይንስ አውር ነው"

አንስታይንን እንኮንነውም ብርሃንን ከቁርዓን ሲፈነጠቅ አይተነዋልና ወጋገኑ በምድር ዙሪያ በርቷልና ግና የደረትን የጎድን አጥንቶች አልፎ ከልቦና ላይ እንብዛም አለመዝለቁ ለምን ይሆን?

ልብ የምታደርጉ እንደሆን ለናንተ ማብራሪያዎችን ገለፁን

አል-ኢምራን 119

# የጭስ ሀይል

በአሜሪካ ውስጥ 52.8 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ሲጋራ ያጨሳሉ፤ ከነሱም መካከል እድሜአቸው 12-17 የሚደርሱት 4.1 ሚሊዮን ይደርሳሉ፡፡

በ World Health Organization (የዓለም የጤና ማኀበር) ዘገባ መሠረት በኢሮ- ውያኑ የዘመን አቆጣጠር 2020 በሲጋራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች አስከፊነታቸው ከኤድስ በላይ የናረ ይሆናል ይላሉ፡፡ ከነዚህም በሽታዎች መካከል የልብ በሽታ፣ ነቀርሳ፣ የመተንፈሳ አካል መዛባት ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡

በዚህ በሲጋራ ቅስፈት በበለጠ ሰለባ የሚሆኑት የሚያጨሱ ሰዎች ሲሆኑ በአጫሳች ዙሪያ ያሉ የማያጨሱ ሰዎች ከ20% በላይ ለበሽታዎቹ የመጠቃት እድል አላቸው፡፡ ጉዳዩ የፍርድ ቤቶችን ዶሴዎች ያጣበበ ቢሆንም ዳኞች 60% የሚሆነውን ሀላፊነት ለአጫሾች ሲበይኑ 40% የሚሆነውን ሀላፊነት በአምራች - አከፋፋዮች ላይ ደንግገዋል፡፡

ከመሰል ሱሰኝነት ብሎም - እራስን በራስ ከመጉዳት አላህ (ሱ.ወ) ይጠብቀን በማለት የጭስን ተዐምራዊ ይዘት ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ በርግጭ ጭስ ሳንባን አቃጥሎ ልብን አላልቶ ለሞት ካበቃ ስነ-ፍጠረታት ሰማይ ምድር ከዋክብት ሁላ አሁን ያሉበትን ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ጭስ ነበሩ ብንሎት ምን ይላሉ? ታዲያ የጭስን ሀይለኛነት አይገነዘቡምን?

ኢንሻ አላህ ይህንን እውነታ ቁርዓንና ሳይንስን በማጣቀስ ለመቃኘት እንሞክራለንና ልብ ይበሉ!

የዘመኑ ሳይንቲስቶች ባደረጉት ያላሰለሰ ጥረት፣ የሌት-ተቀን ልፋት ይህንን መረጃ ለሰው ልጆች ይፋ በማድረጋቸው እሰየው እስብሎ ታላቅ ዋጋ (credit) ሊያሰጣቸው ይገባል፡፡

የ Big Bang እውነታን ስናመለክት በግራሞት ሰረገላ ተሳፍረን የተዓምሩን ብስራት አጢነን እውነታን ከጨበጥን ዛሬም ዳግማዊ እውነታን እነሆ!...

እንደ ሳይንቲስቶቹ አገላለፅ የክዋክብት ጥርቅም (Galaxy) ከመፈጠሩ በፊት ስነ-ፍጠረታት ታላቅ የጋዝ ጥርቅም ነበሩ፡፡ በሌላ አነጋገር ሰማያት፣ ምድር ፀሀይ ጨረቃ ከዋክብት አሁን ባሉበት ሁናቴ ከመገኘታቸው በፊት በጋዝ መልክ ይገኙ ነበር ማለት ነው፡፡ ሁናቴውን ለመግለፅ ጋዝ ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በላይ 'ድኻን' ወይም ጪስ የሚለው የአረብኛ ቃል ይበልጡን ማብራሪያ አለው፡

እንግዲህ ይህንን ሳይንሳዊ አውታ ነበር ቁርዓን ከ1400 ዓመት በትንግርታዊ አናቅጸቹ መካከል በጉልህ ያዘለው፡፡

"ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ኾና ሳለች አሰበ፤ ለርሷም ለምድርም ወዳችሁም ይሁን ጠልታችሁ ኑ አላቸው ታዛዦች ሆነን መጣን አሉ። በሁለት ቀኖችም ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው በሰማያቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን። "

አል-ሰጀዳህ- 11-12

የአላህ ጥበብ ተበሰረ የጥበብ ድርሳኑ ተነገረ የእውነት ሚዛኑ ደፋ ግና ምነው ልብ አልሰፋ? ጌታ እኮ አስፍቶታል።

" ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህም? (አስፍተንልሃል)

አል-ኢሽራዕ - 1

እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል! የጭስን ሀይል ይገንዘብ ከሱስም ይቆጠብ አላህ የተሻለን ያውቃል።

ወደ ፍሬ ሃሣባችን እንመለስና ሳይንስ እንዳመላከተው ከሆነ ሥነ-ፍጥረታት ወደ ቁስ አካልነት የተቀየሩት ከ Big Bang በኋላ ነው ከዚያ በፊት ሀይል ወይም ግዜ አልነበረም ይህ የዘመናዊ Physics እውነታ በቁርዓን መመዝገቡ ይታወሳል።

በ1992 የNASA ሳተላይት ባነፈነፈው ማስረጃ መሠረት የ Big Bang ቅሪቶችን በመመርኮዝ ሥነ-ፍጥረታት ከምንም መፈጠራቸውን አመልክቶናል - እንግዲህ "ሁን" የሚለው የአላህ ትዕዛዝስ? በዚያም ትዕዛዙ ነው ሥነ-ፍጥረት (ሰማያት - ምድርን ያስገኘ)

እርሱ ሰማያትና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው

አል- አንዓም - 101

የምርምሮች ሁሉ አቅጣጫ ወደ matter (ነገር) ካደላ ይህንን (ቁስ - አካልስ) ማን ነው የፈጠረው? በርግጥም ያ የማይሞተው የማይወልደው አላህ (ሱ.ወ) ነው። የፍጥረታት ሁናቴ በሙሉ ወደርሱ የሚያተኩር ነው።

"ነገርንም ሁሉ ፈጠረ እርሱም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው"

አል-አንዓም 121

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክዋክብትን ቀና ብለው አይኖ የቻለውን ይመልከቱ የጨረቃን ድምቀት ይገምቱ የመሬትን ሁናቴ ያስተውሉ እውነትን ያያሉ- እውነትና ንጋት አድረው ይጠራሉና! በቸር እንሰንብት - አላህ የተሻለን ያውቃል።

ጥያቄ አንዳንድ ሰዎች ለምን ታጠፋላችሁ ተብለው ሲጠየቁ የፈለግኩትን የማድረግ መብት አለኝ free ነኝ ይላል ይህ አባባል ትክክል ነውን

መልስ ይህ ስህተት ነው:: አላህን ላለመታዘዝ መብት የላቸውም:: ጌታቸውን የማይታዘዙ ከሆነ የአላህ (ሱ.ወ) ባርነታቸውን ፍቀው የሸይጧንና የፍላጎት (የነፍስያ) ባሪያ ይሆናሉ:: ስለዚህ ዱዓና ዳዕዋ አድርግላቸው::

<u>ወላሁ አዕለም</u>

ጥያቄ ለዘላለም ኑር! ዘላለም ያኑርህ ማለት ይቻላልን?

መልስ ዘላለም ነዋሪ አላህ (ሱ.ወ) ብቻ ስለሆነ አባባሉ የአላህን ባህሪ ስለሚፃረር "ለዘላለም ኑር" ብሎ ለሰው ልጅ መመኘት አይቻልም ምክንያቱም በምድር ያሉ ሁላ ጠፊ ነውና!

"በርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው:: የልዕልና የልግስና ባለቤት የሆነው የጌታህ ፊትም ይጠራል (አይጠፋም) "

አል -ረህማን 26 -27

አንድ የቁርዓን አያ እንጨምርልህና መልሱን እንቋጨው

"ሙሃመድ ሆይ! ካንተ በፊት ለማንም ሰው ዘለዓለም መኖርን አላደረግንም! ታዲያ ብትሞት እነርሱ ዘውታሪዎች ናቸውን?"

አል - አንቢያ - 34

<u>ወላሁ አዕለም</u>

ጥያቄ ፍርሃት፣ ፍርሃት ይለኛው ሰው የሚተናኮለኝ ይመስለኛል እባካችሁ ምከሩኝ

መልስ ሰዎች በተለያዩ ግዜያትና አጋጣሚዎች መሰል ፍርሃቶች ሊገጥሟቸው ይችላሉ ስለዚህ ችግርህ ያለ የነበረ የሚኖር በመሆኑ ብዙ አትደናገር

1. ፍርሃትህ በሃሣብ የሚከሰት (Imangiation) ከሆነ የሥነ -ልቦና ችግር የተጠናወተክ ይመስለናል
2. ፍርሃትህ በሆነ በተከሰተ ነገር ወይም ዱካ ባለው የፍርሃት ምንጭ ከሆነ ከነገሩ ለማምለጥ መፍትሄውን መሻት አለብህ
3. ፍርሃትህ ውሉ ያልታወቀ ጭብጥ የሌለው ከሆነ የፍርሃትህን ምንጭ አብጠርጥረህ ለማወቅ ሞክር

<u>መፍትሔ:</u> - ኢማንህን አጠንክር በአሏህ ተመካ በአላህ የተመካ ፍርሃት ድርሽ አይለውምና ዱዓ አድርግ ወደ አላህ ተጠጋ እርሱ ካንተ ተሻለ ሁናቴ ወደ አንተ ይጠጋሃል ይጎዳኛል ብለህ የምታስበው ሰው ካለም ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ዱዓ አድርግ - ዱዓው በሙስሊም የተዘገበ ነው

አልሏሁምመ ኢክፊኒኒም ቢማ ሺእተ

"አላህ ሆይ! በመረጥከው መንገድ ከነኝህ ሰዎች (አዳጋ) ጠብቀኝ"

አላህ የተሻለውን ያውቃል

ጥያቄ ለህፃናት የሚወጡ ስሞች፣ በህፃናቱ የወደፊት የእድገት ሁናቴና ፀባይ ላይ ተፅእኖ ሊኖራቸው ይችላልን?

መልስ

1. የስሞቹን አወጣጥ በመለኮታዊ ቅኝት ካየናቸው ስሞች መጠሪያ በመሆናቸው ምንም አይነት ተፅእኖ ጥሩ ወይም መጥፎ ገድን አያስከትሉም። ከመሰል መሰረተ-ቢስ አምልእኮ ህብረተሰባችን ይላቀቅ ዘንድ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለብን
2. የስሞቹን አወጣጥ በማህበራዊ ኑሮ ሁኔታ ካየነው ተፅእኖ ይኖራቸዋል። ለምሳሌ " አሽብር" ተብሎ ስም የተሰጠው ህፃን ህብረተሰቡ ስሙን በመመርኮዝ የሚያበሽቀው በለበጣ የሚያናግረው ከሆነ በስሙ በመኩራራት ወይም በማፈር ለስነ-ልቦና ችግር ሊጋለጥ ይችላል።
3. ጥሩ ስም ማውጣቱ ኢስላማዊ ግዴታ ሲሆን ህፃናትም በወሊድ ወቅት የሚጎናፀፉት አስላማዊ መብት ነው። አብደላህ (የአላህ ባሪያ) አብድልረህማን (የመሃሪው ባሪያ) ዋንኛዎቹ ሲሆኑ ሙሃመድ፣ አህመድ ወዘተ የመሣሰሉ ስሞችን ልንሰይም እንችላለን
4. ቃላቶች አረቢኛ ብቻ በመሆናቸው የሚያምሩ እየመሰሉን ከመሰየም ትርጓሜአቸውን ማጤን! ለምሳሌ አስአብ (አስቸጋሪ) አሳቢያ (ቁጣ ደምፍላት) ማለት ሲሆን፣ መሰል ስማችን ማውጣት የለብንም።

   ለማጠቃለል ዘመኑ የመረጃ በመሆኑ የሙስሊምን ስሞች ከነትርጎሜአቸው ያዘሉ መፅሃፍት ከኢስላሚክ Book Store ይገኛሉ ወይም በ Internet የሙስሊም ስሞች ዝርዝርን በመፈለግ የመልካም ስሞችን መምረጥ ይቻላል። በምርጫው ላይ ጥርጣሬ- ካለን ስሙን ከመሰየማችን በፊት የሚያውቁትን በመጠየቅ በቂ ግንዛቤ እናግኝ።

   አላህ የተሻለውን ያውቃል።

ጥያቄ የስደቱ ኑሮ ለኢባዳ (ለአምልኮ) አልመችም እያለን ነው የምትመክሩን ምክር ካለ?

መልስ ወንድማችን ሆይ! በደንብ ይመቻል ለመሆኑ በከተማችን ውስጥ ምን ያልህ መስጊዶች አሉ? በጣም ብዙ! ጁምዓና ጀመዓ በስፋት ይከናወናል ኢድ በሚገርም ሁናቴ በህብረት ይሰገዳል ታዲያ ስደቱ ምን አጠፋ?

አላህን የትም መቼም በድሎት - በሀዘን በርሀብ በጥጋብ፣ መገዛት አለብን።

ኢልም በየቦታው ሞልቷል በየመስጂዱ ኘሮግራም አለ ለመሆኑ የትኛውን ተከታትለሃል? ኢልምን ኢንተርኔት ላይ በጣቶችህ ሰበቃ ልታገኝ ትችላለህ ለመሆኑ ይህንን አድርገሃል?

ሙፊቲህ ሙሃመድ ሲራጅ በየሳምንቱ አርብ ማታ የቁርዓን ተፍሲር (ትርጉም) ብሎም የጥያቄና የመልስ ምርጥ ኘሮግራም አላቸው ለመሆኑ ተከታትለህ ታውቃለህን?

ያለንን አለማወቁ ከከሳሪዎች ያረገናልና ተጠንቀቅ። ማስተባበል ደግሞ ለኢስላም ቦታ የለውምና ንቃ! እንካ የንቃትን ደወል... ከቁርዓን!

"እነዚያ ያመኑት ከአገራቸውም የተሰደዱት በገንዘቦቻቸውና በነፍሳቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው እነዚያ እነርሱ የፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው።"

አል-ተውባህ - 20

የአላህ ቃል - ኪዳን ነው የፍላጎትህን ታገኝ ዘንዳ ያለብህን የማመኻኘት የማስተባበል ግርዶሽ ጣለው ስደት አላህን ከመገዛት አያግድም ስንፍና አንጂ!

አላህ የተሻለውን ያውቃል።

ጥያቄ ለትምህርት ብዬ ከቤተሰቦቼ ተለይቻለሁ መለየቴ ሐላል ነውን ስደቴንስ እንዴት ታዩታላችሁ

መልስ አንድ ሰው ሳይወድ በግድ የሚያከናውናቸው መለያየቶች ይፈቀዳሉ ከነዚህም አንዱ ለዕውቀት (ለኢልም) መሠድድ ነው። ግን ከወላጆችህ ለመገናኘት የምትችለውን ያህል መጣር አለብህ በተጨማሪም በስልክ በ E-mail በደብዳቤ መገናኘቱን አዘውትር! መፃፃፍና መደዋወሉ ናፍቆትን ያስታግሳልና ሁሌም ከነርሱ ለመገናኘት ከመጣር አትቆጠብ አላህ (ሱ.ወ) አላማህን ያሣካልህና ለኡማው ሁሉ ጠቃሚ የምትሆን- ያድርግህ ዕውቀት ብርሃን ነውና!

ጥያቄ ጥፍሬን የመንከስና የመቆርጠም ችግር አለብኝ ይህ ደግሞ በዲናችን የተጠላ ነው ሲባል ሰምቻለሁ ይህንን መጥፎ ልማዴን እንዳቆም የምትመክሩኝ ምክር ካለ

መልስ ጥፍርን የመብላትና መንከስ ሁናቴ የስነ-ልቦና ችግር የተያያዘ እንደሆነ ዶክተሮች ይናገራሉ። ህፃን ሆነሽ ከሆነ ይህንን አመል የጀመርሽው ዲን ያለው የስነ-ልቦና ጠቢብ ብታይ መልካም ነው።

ኢስላም በጥሩ ፀባይ ያንፃል መጥፎ ልማዳዊና መጤ የሆኑ ለኡማው የማይጠቅሙ ባህርያትን ይከለክላል - በኢስላም ከሚጠሉት ባህርያት አንዱ ጥፍርን መንከስ ነው ስለዚህ አላህ ይህንን ባህሪ እንዲያነሳልሽ ዱዓ አድርጊ እጆችሽን ለዚክር አድርጊያቸው ቁርዓን መቅራትን አዘውትሪ ከፈርዱም በሻገር ሱናዎችን አዘውትሪ ኢንሻ አላህ ከኢባዳህ

ጥያቄ ወጣት ባለትዳር ነኝ እሰግዳለሁ ግን ከአይን ዚና መታቀብ ስላልቻልኩኝ የምትመክሩኝ ምክር ካለ

መልስ አላህን መገዛት ቦታ ግዜ የማይወስነው ዘመን የማይሽረው የለት-ተለት ግዴታ ነው:: መለወጥን በመፈለግ ምክርን መጠየቅህ እራሱ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ነው

ምክር 1

ሁሌም የምታከናውነውን ኢባዳ (አምልኮ) ለአላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ብቻ ብለህ አድርገው ለአላህ ተብሎ የሚደረግ ለስኬቱ ጥርጥር የለውምና! አላህ እራሱ በቁርዓን ይህንን አመላክቶናል

ስግደቴም መገዛቴም ህይወቴም ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው በል::

አል-አንዓም- 162

ምክር 2

በትክክል የሚሰገድ ሰላት ከሃጢዓት ሁላ ይጠብቃል ሶላትን የምትሰግደው በፍራቻና በመተናነስ ነውን? ወይስ ግዴታ ስለሆነ ብቻ? የሰላትህን ሁናቴ ማስተካከል አለብህ የሩጫ - የሩጫ ሰላት መስገድ የለብህም ረጋ - ሰከን ብለህ እያስተዋልክ ስገደው ሰላቱ እራሱ ጋሻ ይሆንሃል! እነሆ ጥርጥር የሌለበትን የአንድዬ ጌታ ቃልን

" ሰላትን ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፣ ሰላት ከመጥፎ ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና"

አል-አንከቡት 45

አላህ የተሻለውን ያውቃል

ጥያቄ ምንም ልብስ ሳይለበስ መተኛት ይቻላልን?

መልስ የግል ቦታ ሁሌም መሸፈን አለበት ግዴት ሲሆን በስተቀር ለምሣሌ ገላን ሲታጠብ ለተራክቦ ወዘተ ግን ያለምንም ምክንያት ከሌላ መሸፈን አለበት ቦባህዝ ኢብን ሐኪም ከአባቱ በሰማውና በተናገረው ሀዲስ አያቱ ረሱል እንዲህ ብለው ነበር "የአላህ መልእተኛ ሆይ! የግል ቦታዎቻችንን ምን ማድረግ አለብን? ረሱልም ሲመልሱ ከሚስቶታችሁ በስተቀር የግል

ቦታችሁን ሽፍኑ ከነዚያ ከእቁባቶቻችሁ በስተቀር አንድ ወንድ ከሌላ ወንድ ጋር ሲሆንስ ሌላ ሰው እንዳያየው ማድረግ የምትችሉ ከሆነ አድርጉት ብቻችንስ ስንሆን? አላህ የበለጠ ይገባዋል በአላህ ፊት አይን አፋር ልትሆኑ ይገባል" ቲርሚዝ ዘግበውታል

ከላይ በተጠቀሰው ሀዲስ መሠረት የግል ቦታህን ሳትሸፍን መተኛት አትችልም ለብቻህም ይሁን ከትዳር አጋርህ ጋር ግና በአስፈላጊ ጊዜ የግል ቦታህን (አውራህን) ማገለፅ ይቻላል - አሏህ የተሻለ ያውቃል

ጥያቄ አንድ ሰው ባላደረገው ነገር ስሙ እየጠፋ ለፈተና ቢጋለጥ ምን ማድረግ አለበት?

መልስ የአማኒያን ሁሌም በሁለት ሁናቴዎች ውስጥ ቢሆኑ ይገባል አመስጋኝና ታጋሽ መልካም ሲገጥማቸው አሏህን ያመሰግናሉ ክፉም ሲደርስባቸው ይታገሣሉ! በሁለቱም ክንዋኔዎች መመንዳታቸው የማይቀር ነው!

ስም መጥፋት ዛሬ ባንተ አልተጀመረም አላህ እራሱ የመረጣቸውም ነብያቶች ስማቸው በኃጢተኞች ይጠፋ ነበር - ታላቁ ነቢያችንም (ሰ.ዓ.ወ) ዕብድ ድግምተኛ ተብለው ነበር

ሰብረ አድርግና ከአሏህ አጅርን ጠብቅ በመበደልህ ላንተ አላህ ኃጢዓትህን ይቀንስልሃል:: እራስህን የመከላከል መብትህ የተጠበቀ ነው ንፁህነትህን በማስረዳት ማረጋገጥ ትችላለህ ስምህን የሚያጠፋውን ሰው አላህን እንዲፈራ ምከረው ወይም በሌላ በበሰለ ሰው እንዲመከር አድርገው አላህ መፍትሆን ይሰጥሃል በሠብረ በርታ ደግሞም ሰዎች ምን ይሉኛል ስሜ በመጥፋቱ ብለህ አትጨነቅ ሰዎች ሁሌ የሚያስቡት ስለ ራሣቸው ሃጃ በመሆኑ አንተን ይረሱሃል

ጥያቄ 1 ጡትን ኘላስቲክ ሰርጀሪ አድርጎ ማሳደግ ይፈቀዳልን?

መልስ ጡትን ማሣደግ የተከለከለ ነው የአሏህን አፈጣጠር መቃወም ይሆናልና የትንሽ ጡት ባለቤት መሆን የጤና ችግር አለመሆኑን ልብ በይና ያለሽን ውደጂ

ጥያቄ 2 Vegetarian መሆን አትክልት ብቻ መብላት ሐራም ነውን?

መልስ አትክልት ብቻ መብላት ሐራም አይደለም:: አላህ የፈቀደውንም ሥጋ ሀራም ነው ብሎ ማሰቡ ሀራም ነው እንጂ! vegetarian መሆን ከፈለግሽ ተመጣጣኝ ኘሮቲኖችን መግኘት መቻልሽን Tutrionist ማማከርሽን አትርሺ!

ጥያቄ 3 የኮምፒውተር መረጃ (Software) ና መፅሀፍን ያለ አታሚው ፈቃድ ኮፒ ማድረግ ሀራም ነውን?

መልስ ማንኛውም ምሁራዊ ሀብት መፅሀፍ፣ የቪዲዮ ካሴት የቴፕ ክር፣ የኮምፒውተር መረጃ ያለባለቤቱ ፍቃድ ኮፒ ማድረግ ሐራም የተከለከለ ነው። ግን የሕዝብ የሆኑን ነገሮች ለጥናት ለምርምር ኮፒ ማድረግ ትችላለህ - አላህ ይርዳህ!

ጥያቄ 4 ሙስሊም ከሆንኩ 13 ዓመቴ ነው በልቦናዬ ሁላ ኢስላምን እወዳለሁ ግና አናቴ ከ38 ዓመት በፊት ያለ ጋብቻ የወለደችውን ልጅ ለጉዲፈቻ (adoption) መስጠቷን አወቅኩኝ። እርሱ ወንድሜም አሁን ሊተዋወቀኝ ይፈልጋል እንዴት አድርጌ ነው በኢስላማዊ መርህ የምተዋወቀው? ለልጆቼስ ምን ብዬ ልንገራቸው? እንደ ወንድምስ ላየው እችላለሁ?

መልስ እስላማዊ ህግ ከርሱ እንድትተዋወቂ አያግድሽም ወንድምሽ ነውና! እሱ (ወንድምሽ) ያጠፋው ምንም ጥፋት የለም እናትሽና አጋሯ እንጂ! አንቺም ሆንሽ ልጆችሽ በሸሪዓው ህግ ልታገቡት አትችሉም። ለልጆችሽ ያለ ጋብቻ የተወለደ አጐታችሁ ነው ብለሽ አትግለጪ አያታቸውን መጥፎ ናት ብለው ሊያስቡ ይችላሉና! በተረፈ አላህ ይጨመርበት።

ጥያቄ 5 እንግሊዝኛ የማይችለው ጎረቤቴ በ x-mass የቢራ ስጦታ አመጣልኝ መቀበል እንደማልችል ስነግረው ስላልገባው የቤቴ ደረጃ ላይ ጥሎት ሄደ እኔም እያንዳንዱን ቢራ ከፍቼ ሲንክ (Sink) ውስጥ ደፋሁት የወሰዱኩት እርምጃ ትክክል ነበርን?

መልስ ጎረቤትህን ለማስረዳት ሞክረህ ካልገባው እንኳንም ወስደህ ደፋኸው በረንዳ ላይ ብተወው ሌላ ሰው ወስዶ ይጠጣው ነበርና! እዚህ ላይ ልብ በል እርምጃህ የሚታሰበው በኒያህ ነውና። ጎረቤትህ ያለምንም ምርጫ እንደተወህ እርግጠኛ ሁን። ሁሌም ከመጠጥ ራቅ፣ ሁሌም ሌሎች ከመጠጥ እንዲርቁ አስተምር ጎጂና ሐራም ነውና!

ጥያቄ አንዳንድ ሰዎች - እዚሁ አሜሪካ ውስጥ ሐራም ሲሰሩ ለምን ትሰራላችሁ ተብለው ሲጠየቁ 'እነ-እከሌ' 'እነ-እከሌ' ይሰሩታል ብለው ያስተባብላሉ አባባላቸው ትክክል ነውን?

መልስ እነ እከሌ እሳት ውስጥ ዘለው ቢገቡ እነርሱም አብረው ይገባሉ እንዴ? የተሳሳተና መሠረት የሌለው አባባል ቢሆንም ህብረተሰባችንን በጣም እየጎዳ ያለ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ታላቅ ትኩረትም ሊሰጠው ይገባል።

እራስን መምሰል ታላቅ ፀጋ ነው በመልካም ማዘዝ በመጥፎ መከልከሉ የታዘዘ መሆኑን ልናመላክት እንወዳለን።

" በምድርም ካሉት ሰዎች አብዛኛዎቹን ብትተከተል ከአላህ መንገድ ያሳስቱሃል ጥርጣሬን እንጂ ሌላን አይከተሉም እነርሱ የሚዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም "

አል- አንዓም 116

ከላይ የተጠቀሰውን የቁርዓን አያ በመመርኮዝ ሀላል - ሐራም በቁርዓን በሐዲስ የተበየነ በመሆኑ ሐይማኖታዊ ፈለግን መከተል ከሚያጠራጥሩ ነገሮችም መራቅና ወደ ሐላሉ ወደ (ተፈቀደው) መዘንበል::

በማሳሳት ጎራ ላይ የተሰማሩና ጠሞ-በማጥመም የተካኑ አያሌ ሕዝቦች ቢኖሩም እነርሱ የጨበጡት የህይወት መመሪያ ከከሳሪዎች ስለሚያስመድባቸው ሁሌም መንቃት ሐራምን ከሐላል አብጠርጥሮ ለማወቅ መጣር!

አላህ የተሻለውን ያውቃል

ጥያቄ ለሰዎች በጎ እንዲሰሩ መክራለሁ ከሃጢዓትም እንዲርቁ አስጠነቅቃለሁ እራሴ ግን ለሌሎች አትፈፅሙ የምለውን ሀጢዓት አንዳንዴ አደርጋለሁ ከሐይማኖቱ አኳያ ሁኔታዬን እንዴት ታዩታላችሁ

መልስ ሰዎችን እየመከሩ ሐጢዓት መፈፀም የተፈቀደ አይደለም በኢስላም በጣሙን የተጠላ ነው:: ማስረጃውንም ከቁርዓን እነሆ!

"የማትሰሩትን ነገር መናገራችሁ አላህ ዘንድ መጣላቱ ታላቅ:: "

አል-ሶፍ - 3

ወንድማችን ሆይ! ህሊናህን ገምግመውና የተጠቀሰውን የቁርዓን አንቀፅ በደንብ አጥናውና የምትናገረውን ለማድረግ ቆርጠህ ተነሣ አንተ በመቀየርህ ብሎም ሌሎች ባንተሳቢያ በመቀየራቸው አይንህ ሊያየው፣ ጆሮህ ሊሰማው፣ አዕምሮህ ሊገምተው ከሚችለው በላይ የላቀ ምንዳን በጌታህ በረከት ያስገኝልሃል! ለማሳረጊያም ሌላ የቁርዓን አያን እነሆ!

አናንተ መፅሃፉን የምታነቡ ሆናችሁ ሰዎችን በበጎ ሥራ ታዛላችሁን? ነፍሶቻችሁንም ትረሳላችሁን? (የድርጊታችሁን አስከፊነት ተገንዝባችሁ አትታረሙምን?)

አል-በቀራህ - 44

አላህ የተሻለውን ያውቃል

ጥያቄ አንዳንድ ጓደኞቼ የሚያሙኝ እየመሰለኝ ከበር ልጥፍ ብዬ ላዳምጣቸው ወይም መቅጃ (Recorder) ደብቄ ልቀዳቸው እፈልጋለሁ ድርጊቴን እንዴት ታዩታላችሁ

መልስ ድርጊትህ ትክክል አይደለምና ሳይጠናብህ ቶሎ ተመለስ ምክንያቱም፡-

1. ህገወጥ ድርጊት ነው:: ከህግ መፃረር የለብህም
2. በቁርዓን የተከለከለ ነው
3. ወዳድ ጓደኛን ታጣና የከፋ ይገጥምሃል

ወንድማችን ሆይ! ትንሽ ረጋ - ሰከን - ብለህ አስተውል ቢያሙህ የሰውን ሥጋ የበሉ እነርሱ! ሐጢዓት ላይ የሚወድቁ እነርሱ 'ክፋ ለራሱ ደግ ለራሱ' ሲባል አልሰማህምን? ሲያሙህ ብትሰማ እንኳ በጥርጣሬ ሆድህ ይሻክራል - ጓደኛም ታጣለህ! (ኢንሻ አላህ) አሏህ (ሱ.ወ) ቀናውን መንገድ መርቷቸው የልብ ወዳጆች ሊሆኑ ይችላሉ:: በተጨማሪም ጥሩነት የሚጀምረው ከራስ በመሆኑ ቀጥተኛውን ጎዳና ይመራቸው ዘንድ ሁሌም በፀሎትህ አትርሳቸው::

ለመሆኑ ለምን በጥርጣሬ መብከንከንህ በዛ? ምን የሚያሳማ ተግባር ፈፅመሃል? እነርሱስ ሲያሙህ ሰምተሃል? በጥያቄህ መሠረት የጎላ ችግር ያገኘነው አንተ ዘንድ ነው አላህ የከለከለውን ለመፈፀም አስበሃልና "እናንተ ያመናች ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ ከጥርጣሬ ከፊሉ ሃጢዓት ነውና! ነውርንም አትከታተሉ (አትሰልሉ) ከፊላችሁ ከፊሉን አይማ አንዳችሁ የወንድሙን ሥጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? ( ላቱን) ጠላችሁትም (ሐሜትንም ጥሉት) አላህንም ፍሩ አላህ ጸጸት ተቀባይ አዛኝ ነውና:: "

አል ሑጅራት - 12

ታዲያ ችግሩን ማን ጋር አገኘሽው በሃሣባዊ እይታ (Imagination) እራስህን ለስነልቦና ችግር እንዳትዳርግ አሁኑኑ ተመለስ

አላህ የተሻለውን ያውቃል

ጥያቄ 2 ኢስላማዊ ፅሁፍ ያለባቸውን መፅሔትና ጋዜጦች ለእቃ መጠቅለያነት ወይም በምግብ ጠረጴዛ ላይ እንዳይንጠባጠብ አንጥፈን ልንጠቀምባቸው እንችላለን? ከተጠቀምንባቸውስ በኋላ ምን ልናደርጋቸው ይገባል::

መልስ ኢስላማዊ ፅሁፍ ያለባቸውን ጋዜጦችና መፅሔቶች ለጠረጴዛ ንጣፍነት ወይም ለእቃ መጠቅለያነት ለመጠቀም ቀርቶ ፅሁፎቹን ማንገላታትና በማይሆን ቦታ ማስቀመጡ የተከለከለ ነው:: የአሏህን ስምና የቁርዓን አያን ያዘሉ ከሆነ:: ከተጠቀምንባቸውም በኋላ በምቹ ቦታ አስቀምጣቸው ወይም በእሣት አቃጥላቸው ወይም በንፁህ አፈር ውስጥ ቅበራቸው:: አልያም በየመስጂድ ኢስላማዊ ፅሁፎች ማጠራቀሚያ ሊኖር ስለሚችል ጎራ በልና ማጠራቀሚያ በርሜል ውስጥ አኑራቸው::

ጥያቄ ምንም መተዳደሪያ የሌለው የሙስሊም ቤተሰብ የኢንተርኔት አገልግሎት በመስጠት ገቢ ቢያገኝና ቤተሰቡን ቢረዳ ሀራም ነውን?

መልስ ኢንተርኔት ለሀራምም ለሀላልም ሁናቴዎች ግልጋሎት አለው የኢንተርኔቱን አካባቢ ተቆጣጥረህ ሰዎች ሀራም ነገሮችን እንዳይጠቀሙ ማገድ የምትችል ከሆነ ገቢው ሀላል ይሆናል:: ግን መጥፎ ነገሮችን ሲሰሩ ግድ የማይሰጥህ ከሆነ ሀራምን የማታቆም ከሆነ ኃጢዓት ላይ ስለምትወድቅ ገቢው ሀራም ይሆናል::

ጥያቄ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ጎረቤቶች አሉኝ፣ አንዳንዳቹን ብረዳቸው በገንዘቡ ምግብ ብቻ ሣይሆን መጠጥ ወይም (አደንዛዥ ዕፅ) ሊገዙበት እንደሚችሉ አውቃለሁ፡ እንዴት አድርጌ በሀላል መልኩ የጎረቤቶቼን ሀቅ መወጣት እችላለሁ::

መልስ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለምሣሌ ምግብ አልባሣት ልትገዛላቸው ትችላለህ:: ወይም ከሱቅ ይዘሃቸው ውጣና ሀላል ነገር እንዲገበያዩ አድርገህ ወጪውን አንተ ክፈል:: ምከራቸው - የአሏህ ቅጣት እንዳለም አስጠንቅቃቸው ወደ ኢስላምም ጥራቸው የጎረቤት ሃቅ ታላቅ ነውና!

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሶስቱም የሀዲስ ዘጋቢዎች በተስማሙበት ሃዲስ እንዲህ ብለዋል " ጂብሪል በተደጋጋሚ ስለጎረቤት ሃቅ መከረኝ የኔ ወራሾች ሊያረጋቸው ነው ብዬ እስካስብ ድረስ"

እንግዲህ እዚህ ላይ ልብ ልትለው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ኢስላም ጉርብትናን አስመልክቶ ፍትሃዊ የሆነውን ድንጋጌ ለሰው ልጆች ሁላ ማዕደቁን ነው!

<u>ወለሁ አዕለም</u>

ጥያቄ ረጅም እድሜ ይስጥህ ብሎ ለሰዎች መመኘት ይቻላልን?

መልስ ለሰዎች ኢባዳ (አምልኮ) የሌለበት ረጅም ዕድሜ ልንመኝላቸው አይገባም:: ምክንያቱም በህይወት ዘመናቸው ክፉ ወይም ደግ ሲሰሩ ይችላሉና - ነው:: መጥፎ ሰዎች ማለት ረጅም ዕድሜን ተጎናፅፈው ክፉ መስራትን የማያቋርጡ ናቸው:: ስለዚህ "አላህን የምትታዘዝበት ረጅም ዕድሜ ይስጥህ" ማለቱ ጥሩ ነው::

" ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ - አልፈጠርኳቸውም"

አልዛሪያት-56

ወንድማችን ሆይ! ስለ እድሜ ካነሣህ አይቀር ከአገራችን ኢስላማዊ ስነፅሁፍ ሀብት (መንዙማ) የተቀነጨበ ግጥም እናሰማህና የዛሬውን የጥያቄና መልስ ዝግጅት እናሣርግ፡፡

ይነጋል እያሉ እያደር ይመሻል
እየመራረጠ ምርጦቹን ያነሣል፡፡

ጥያቄ ባለንበት ዘመን የ cell phone (የእጅ ስልክ) አጠቃቀም በጣሙን እየሰፋ መጥቷል፡፡ በ cell phone ውስጥም የቁርዓንን ድምፅ ማስገባት ይቻላል ወይም ሰው ደውሎ ከቁርዓን እየቀራ መልዕክት ሊተው ይችላል፡፡ ... ይህን ስልክ ይዞ ወደ መፀዳጃ መግባት ይቻላልን?

መልስ እነዚህን ስልኮች መፀዳጃ ይዞ መግባት አይከለከልም፡፡ ቁርዓን ከተቀዳባቸው እንጂ የታተመ የቁርዓን አያን አይዝምና ነው፡፡ ወደ መፀዳጃ ሲገባና ሲወጣ የሚደረጉትን ፀሎቶች ከማድረግ አትቆጠብ አላህ የተሻለውን ያውቃል- ቴክኖሎጂውን አስመልክቶ ለጠየቅከን ጥያቄ እናመሰግናለን፡፡

ጥያቄ የሀያ ዓመት ወጣት ነኝ፡፡ ብዙ የመሣቅ ችግር አለብኝ በሥራ ገበታላይም ይሁን ከሰው ጋር አልያም ብቻዬን ብዙ ግዜ እስቃለሁ ለዚህ ችግር የምትመክሩኝ ምክር ካለ?

መልስ ብዙ መሣቅ የሙስሊምን ልብ እንደሚጎዳ ምንም ጥርጥር የለውም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ብዙ ስለመሣቅ አስጠንቅቀውናል በትርሚዝና በኢብነ ማጃህ በተዘገበው ሀዲስ እንዲህ ብለውናል "ብዙ አትሳቁ ብዙ መሣቅ ልብን ያደርቃልና"

ስለዚህ አላህን በምትፈልገው ቋንቋና ቃላት ጠይቀው ለምንው ተናናሽ ልቦናንና አንደበትን ብሎም እርጥብ አይኖችን ሰጥቶህ ዱዓህ ተቀባይነት አግኝቶ ፊውስን ትጎናፀፊው ዘንድ ቁርዓንን በብዛት አንብብ ተፍሲሩንም (ትርጎሜ) ለማወቅ ሞክር፣ የምትችለውን ያህል የትም ይሁን መቼ ዚክር አላህን አወድስ እስቲግፋር አድርግ፡፡

ችግርህ ካልተወገደ ከላይ የተቀሱትን ኢባዳዎች በማከናወን የስነ-ልቦና ጠበብትን ብታማክር ችግር የለውም ዲኑን ያወቀ ጠቢብ ብታገኝ ደግሞ ላንተ የተሻለ ይሆናል ለዘመኑ ለህክምና ጥበብ ኢስላም ብዙ አስተዋፅኦ በማድረጉ ጠቢብን መሻት ችግር የለውና- አላህ (ሱ.ወ) ያብህን ችግር ያስወግድልህ አሚን

ጥያቄ ከመግሪብ በኋላ ቤት መጥረግ በረካን ያነሳል ሲባል ሰምቻለሁ ይህ ትክክል ነውን፡፡

መልስ ማን እንዳለሽ ባናውቅም ባህላዊ ተረት ይመስለናል ስለጡሃራ (ንፅህና) በስፋት የሚያስተምረው ኢስላም ንፅህናን አይቃወምም ቤትሽን ከመግራብ በኋላ መጥረግ ትችያለሽ እንዲህ አይነት ጎጂ ባህል በኢስላም ቦታ የለውም

ጥያቄ አንዳንዴ ልቤ ንፁህ አይመስለኝም እራሴን እንደተንኮለኛ በመቁጠር የህሊና ፀፀት ይሰማኛል ንፁህ የጠራ ልቦና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ብትጠቁሙኝ

መልስ ብረት እንደሚዝገው ሁሉ ልብ ይዝጋል ነብዩም (ሰ.0.ወ) ልብን የሚያጠራ ምንድን ነው ተብለው ተጠይቀው ነገር ሲመልሱም በተደጋጋሚ ቁርዓን መቅራትና መዘከር (ውዳሴ ማከናወን) ብሎም አላህን ሁሌም የትም ይሁን መቼ ማስታወስ፡፡

ልቦናን ከሚያቆሽሹ ነገሮች ዋነኛዎቹ የንግግርን ስርዓት አለመጠበቅ ሀሜትን ማዘውተር ዋንኛዎቹ ሲሆኑ ምላስህን ተጠንቀቅ ስተናገር አላህን ፍራ ወደ አላህ ቅረብ እርሱ ብዙ ይቀርብሃልና በተደጋጋሚ ዱዓ አድርግ ከቻልክ ብቻህን ስትሆን ኃጢዓትህን አስታውሰህ አልቅስ አብሽር! "የህሊና ፀፀት ይሰማኛል" ብለሃል ፀፀትን ማግኘቱ ጥሩ ምልክት ነው ብዙዎች አሉ አይናቸውና ልባቸው ታውሮ ፀፀት- ንሰሃን ያላገኙ! በርታ አላህ ካንተ ጋር ይሁን!

በውሸት እምላለሁ

ጥያቄ እያወቅኩኝ በውሸት ወላሒ ብዬ ብምል ኃጢዓት ነውን?

መልስ አዎ! ታላቅ ኃጢዓት ነው! የጌታን ስም እንዴት በውሸት ትጠራለህ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ጥያቄህን ሱረቱል አልማኢዳህ ውስጥ ቁጥር 89 ላይ መልሶት ነበር

> "አላህ ለመሀሎቻችሁ በውድቁ አይዛችሁም ግን መሃላዎችን ባሰባችሁት ይይዛችኋል"

ስለዚህ ወንድማችን ከተጠያቂነት ስለማትድን ተጠንቀቅ ለመሆኑ ለምን ትዋሻለህ መዋሸት የፈሪነት ምልክት ነው የእውነት ደግነቱ ልታስታውሰው አይገባም የውሸት ክፋቱ ሁሌም እርሱን ማስታወስ አለብህ እንግዲህ ሐቁን በተጠየቅክ ቁጥር በውሸት ከማልክ በኪሳራ ላይ ነህና ተመለስ፡፡ ለማህበራዊ ችግሮችና መንስኤቸው ፍቱን መድሃኒት የሆነው ኢስላም በመሃላ ቀበኞች ላይ ከ1400 ዓመት በፊት ያፀደቀው ህግጋት ነበር ከላይ የጠቀስነውን የቁርዓን አያ ተከታይ ክፍል እነሆ!

"ማካካሻው (ባፈረሳችሁት ግዜ) ቤተሠቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው ምግብ ዐስርን ምስኪኖች ማብላት ወይም እነሱን ማልበስ ወይም ጫንቃን ነፃ ማውጣት ነው። (ከተባሉት አንዱን ያላገኘም ሰው ሶስት ቀኖችን መጾም ነው። ይህ በማላችሁ ግዜ የመሃሎቻችሁ ማካካሻ ነው። መሃሎታችሁን ጠብቁ እንደዚሁ አላህ ለናንተ አንቀጾችን ያብራራል እናንተ ልታመሰግኑ ይከጀላልና።)

አል-ማኢዳህ 89

እንግዲህ የመሃላን ህግጋት ያመላከትን ይመስለናል አንተም እንደበትህን አዕድተህ - ንስሃ ገብተህ ለሌሎች ዳዕዋ (ጥሪ) እንደምታረግ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን! ወንድማችን ሆይ! ሁሌም የእውነት ጓደኛሁን ሁሌም ወደ እውነት ተጠጋ 'መዋሸት የተከለከለ ነው ቅንጣት ታክል ' እንኳን ቢሆን ብለዋል ታላቁ ነብይ (ሰ.0.ወ) አላህም 'ወዮላቸው ለዋሾች እያለ' አስጠንቅቋል። ዳግማዊ የምስራችን እነሆ!... አላህ አውነት ነው ነቢ እውነት ናቸው... ሞት እውነት ነው... ጀነትና ጀሃነም እውነት ናቸው... አንተም እውነት ተናገር! በውሸት አትማል... አላህ የተሻለን ያውቃል።

ጥያቄ ባለትዳር ነኝ የልጆች አባት ነኝ። በመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት በትዳሬ ደስተኛ ነበርኩ ባለቤቴ በፀባይዋ በሙያዋ በዲኗ ሁሉንም ያሟላላት ቢሆንም ለርሷ ያለኝ ፍቅር እየቀነሰ ነው ቆንጆ ባለመሆኗ እርሷ ደግሞ በጣም ትወደኛለች። ሌላ እንዳላገባ ገንዘብ የለኝም መበደርን እፈልግና ዘላለም በድህነት እኖራለሁ ብዬ እሰጋለሁ ልፈታት አስብና የልጆቼ ጉዳይ ያሳስበኛል - ይህ ያለሁበት ሁናቴ ስለሆነ - ከጭንቀት ገላግሉኝ

መልስ

1. ያለብህ ችግር ሌላን ሚስት የማግባት ወይም የአሁኗን ሚስትህን የመፍታት አይደለም - የገንዘብ ችግር ይመስለናል - አቅሙ እስከሌለህ ድረስ አላህ የባረከልህን ሚስት ጠበቅ አድርጋት
2. ነገሮቹን በተለያዩ አቅጣጫ ተመልከት በዚች በውድ ሚስትህ ላይ ብዙ ጥሩ ነገሮችን ታይባታለህ እንዴት እንደምታከብርህ እንዴት እንደምትንከባከብህ ታዲያ ይህ ከቁንጅና አይበልጥምን? ዋነኛው እኮ ፀባዩ ነው
3. እንግዲህ ይህች ባለቤትህ 75% አሟልታልሃለች አንተ ደግሞ 25% ፍለጋ ወደሌላ ልትሄድነው ሰባ አምስቱን ጥለህ እና አንደው

ቆንጆም ልጅ ብታገባና ባታከብርህ ሰነፍ ብትሆን ገንዘብ አባካኝ ብትሆን ምን ይውጥሃል ወንድማችን ሆይ! ይችን ውድህን ቁንጅናዋን ለአመታት ተደስተህባት ስታበቃ ዛሬ በወሊድ ወዟም ደንግባቷ ቢጠፋም የአንተን ልጅ ለማሣደግ ደፋ ቀና ስትል -ፍቅር አለቀብኝ ትላለህን የልጆችህን እጠፈንታ ምን ታረገው?

4. ከጭንቀት ገላግሉኝ ብለሃል? ምርጫውን ሰጥተንሃል 75% አግኝተሃል 25% ፍለጋ ለማግኘት እየተመኘህ ነውና መልሱን አንተ መልሰው? እኛ የምንልህ ያለህ ጠበቅ - ጥንቀቱን ለቀቅ ተግባባን?

ጥያቄ ነብዩ (ሰ.0.ወ) እናት እንደልነበራቸውና እናታቸው አሚናህ በልጅነታቸው እንደሞቱባቸው ሰምቻለሁ 'እናቴ' እያሉ ሌላን ሴት ሲጠሩ ቂሳ በመስማቴ ይህች እናቴ ያሏት ሴት ማን ናት?

መልስ በረካ ወይም ኡሙ አይመን ትባላለች ምንጯም ከኢትዮጵያ ሲሆን የነቢ እናት የአሚናህ አፅናኝ የነበሩና አሚናህም በደንገት ሲሞቱ ነብዩን በአደራ የተረከቡት አብዛኛውን ህይወቷን ከነቢ ጋር ነው ያሳለፈችው በተለይ የጠላቶችን ሴራ ለማደናቀፍ መረጃ በማሰባሰው ነብዩ በጀነት ውስጥ ቦታ አለሽ ያሏት 'ያ ኡማህ' እናቴ እያሉ ይጠሯት የነበር- ኢትዮጵያዊት ናት በረካ!

ነቢ ሲወለዱ በረካ ክንድ ላይ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፉት

ጥያቄ ልብስ ሳይለበስ እርቃነ ስጋ መተኛት ይቻላል?

መልስ የግል ቦታ ሁሌም መሸፈን አለበት፡፡ ግዳታ ሲሆን በስተቀር ለምሳሌ ለተራክቦ ገላን ለመታጠብ ወ.ዘ.ተ ባህዝ ኢብን ሐኪም ከአባቱ ሰምቶ በተናገረው ሐዲስ አያቱ ረሱልን (ሰ.ወ) እንዲህ ብለው ጠይቀው ነበር

" የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የግል ቦታዎችን ምን ማድረግ አለብን?" ረሱል ሲመልሱም "ከሚስቶቻችሁ በስተቀር የግል ቦታዎችን ሸፍኑ አሉ"

"ከሌላ ወንድ ጋር ሲሆንስ?"

"ሌላ ሰው እንዳያየው ማድርግ የምትችሉ ከሆነ አድርጉት"

"ብቻችንን ስንሆንስ"

"አላህ የበለጠ ስለሚገባው በአላህ ፊት አይን አፋር ልትሆኑ ይገባል" ሐዲሱን ቲርሚዚ ዘግበውታል

ከላይ በተጠቀሰው ሀዲስ መሠረት የግል ቦታህን ሳትሸፍን መተኛት አትችልም! ለብቻህም ይሁን ከትዳር አጋርህ ጋር! ግና አስፈላጊ በሆነበት ወቅት የግል ቦታህን (አውራህን) መግለፅ ትችላለህ

ወላሁ አዕለም!

ጥያቄ የሰራሁት ሥራ ሁሌ ያስጨንቀኛል! ትክክል መሆን አለመሆኔን ንገሩኝ:: ገና እንዳገባሁ ባረግዝም በተፈጥሮ ምክንያት (ያስወርደኛል) ከዚያ በኋላ በተፈጠረብኝ ጭንቀት እርግዝናን እየፈራሁ ኪንን ብውጥም እኔ እንዳልኩት አልነበረምና የሶስት ልጆች እናት ሆንኩኝ:: ጭን ለአላህ ወይም ለኡለሞች ማማከር ሲገባኝ ለዶክተር ብነግረው ከምርጫዎቹ አንዱ ማህጸኔን ለዘላለም መዝጋት ስለነበር ተስማማሁኝ - ሆነም!... ይጨንቀኛል ርዱኝ

መልስ አይዞሽ እህታችን! ቁርዓን ሀዲስ ለሁሉም ጭንቀት ፈውስ ናቸውና! በርግጥ የሰራሽው ሥራ ትክክል አይደለም በሙስሊም ምሁራን (ኡለማ) ፈትዋ መሠረት ማርገዝ የናትየዋን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑ በታማኝ ሃኪም ተረጋግጦ በማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ - ማህፀንን ማበላሸት ሐራም ነው! ስለምን ካልሽ?

1) ከሐዲስ ይቃረናል

በቡኻሪ ዘገባ መሠረት በማቂል ኢብነ ያሲር (ረ.ዓ) በተነገረው ሀዲስ ረሱል እንዲህ ብለው ነበር "አግቡ እነዚያን አፍቃሪና ወላድ የሆኑትን፣ በሕዝባቹ ፊት በቁጥራችሁ አንድኮራ"

2) ከቁርዓን ይቃረናል

አላህ የሰጠን ኒዕማ (ፀጋ) ግላዊ ደስታን ከማስገኘቱም በሻገር የኖሩት ሲሞቱ ሌሎች የሚተኩበት የፍጡራን በር ነው::

"ጥቂቶችም በነበራችሁና ባባዛናችሁ ግዜ አስታውሱ!"

አል- አዕራፍ - 86

እንግዲህ ያ የፍጡራን በር ነው የተዘጋው በርግጥም ሐራም ነው:: መጨነቁ ጥሩ ስሜት ነው:: ይብላኝነት በሰራው መጥፎ ሥራ ለማይጨነቅ ሰው - <u>እህታችን ሆይ</u>! አይዞሽ ረጋ- ሰከን በይና ፊትሽን ወደ አላህ መልሺ! አንዳንዴ እናት መጨከኗን ባንቺው ምሳሌ አድርገሻል:: ግን አላህ (ሱ.ወ) መሃሪ አዛኝ የሆነ ጌታ ነው:: ማረኝ በይው ተውበት (ንስሃ) አድርጊ - ከጭንቀትሽ ትፈወሽ ዘንድ

ወላሁ አዕለም!

ጥያቄ ከዘመኑ የሳይንስ ትምህርቶች በአላህ ዘንድ አጅር የሚያስገኝ ትምህርት ካለ ብትጠቁሙኝ::

መልስ መማር በኢስላም በጣም የሚደገፍና የሚበረታታ የዲንን ኢልም ለማግኘት ሊሚጥር በአላህ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አጅር ሲኖረው! ምንጬ

በአያሌው ኢስላም ወደሆነው የሳይንስ ጥናቶች መዘንበሉም ለሰው ልጆች ደህንነት ከሆነ - ያስመነዳል።

ለምሳሌ፡- Biology ላይ የተሰማራ ሰውን በትጋት ለሚሰራ ብሎም Chemistry አጥንቶ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮችን በመፈብረክ ለሰው ልጆች ቤዛነት ያበረከቱ ፈጣሪው የሚችረው ምንዳ ስለሚኖር ወገናችን በሁሉም መስክ የትምህርትን ዱካ በመከተል የሰናይን ምግባርን ሰንደቅ ያውለበልብ ዘንድ እንጣጣራለን

ወላሁ -አዕለም!

ጥያቄ የጥርስ በሩሽን በጥርስ ሳሙና ጋር መጠቀሙ ሱና ለሆን ይችላልን?

መልስ ንፅህና በኢስላም ከፍተኛ ቦታ አለው። ለዚያም ነው በነብያዊ ምሪት 'ንፅህና የእምነት ግማሽ ነው የተባለው።' የተፈጥሮ መፋቂያን መጠቀሙ ለጥርስና ለአፍ ጤንነት አሌ የማይባል ጠቀሜታ እንዳለው ሳይንሳዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሰፋ ያለ ዘገባ እንኻ አላህ ለወደፊቱ ይዘን እንቀርባለን።

ማንኛውም ሙስሊም የጥርስ ብሩሽንና ሳሙንና ቢጠቀም የንፅህና ክፍል በመሆኑ ጥርጥር የሌለውን ጠቀሜታ ያገኛል ስለዚህ የተፈቀደም ነው።

ትክክለኛ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና የሆነው የመፋቂያ እንጨት መጠቀም ስለሆነ አንተም የዚህን ምንዳ ለመጎናፀፍ በርታ እንልሃለን። የመፋቂያ እንጨት የት ይገኛል የሚል ጥያቄ ከተነሳ የተለያዩ የሐላል መደብሮችንና አንዳንድ የኢትዮጵያውያን ሱቆች መቃኘት ይቻላል።

ወላሁ አዕለም

# የቁርዓን ስነፅሁፋዊ ቅኝት፤ በሳይንስ ሲገመት

ስነፅሁፍና ስነ ግጥም የፈጠራ ችሎታን አንፀባራቂ ናቸው፡፡ በማንኛውም ባልህና የአኗኗር ዘይቤ በቀደምት ዘመናት ስነ-ግጥም የበላይነቱን ቦታ ተጎናፅፎት ቦታውን ለአሁኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በማቀዳጀት ቀጣይ የፈጠራ ተግባራ ሆኗል፡፡

ሙስሊም ያልሆኑ ምሁራን እንኳ የቁርዓንን ስነ-ፅሁፋዊ ምጥቀት ተወዳዳሪ አልባ መሆኑን፣ የአረቢኛው አናቅፅ ምጠቀትን መላበሱን ይስማማሉ፡፡ በአንፃሩ ቁርዓን ይህንን እውነታ በገሃድ ለማስረፅ የመርታት ብስራቱን በአናቅፁ አመላክቷል፡፡

በቀራህ 23-24

እነሆ ቁርዓን በግልፅ የውድድር ጥሪውን ያቀርባል፤ እነዚህ ምጠቀትን የተጎናፀፉ ፀሃፍት 'ሎሬት' የሚባል የማዕረግ ኒሻንን በጅ በደጅ ያደረጉ አያሌ መፅሃፍትና በመድረክ ላይ የታዩ ትያትሮችን የደረሱ አንድ የቁርዓን ሱራ (ምዕራፍ) ያመጡ እንደሆነ? ይህን መሰል የግጥሚያ ጥሪ በተለያዩ የቁርዓን አናቅፅ ተጠቅሷል፡፡ ያማረ አንደበተ-ርቱዕነት፣ ጥልቅ ሰምና ወርቅ ያለው ታሪክን፣ ወቅታዊ ሁኔታን የወደፊት ትንበያን የሚገልፅ ይገኝ እንደሆነ? ዳሩ ቁርዓንን በስነ ፅሁፋዊ ቅኝት የሚረታ ባለመገኘቱ ቁርዓን የአሸናፊነት ሰንደቁን ማውለብለቡን ከጀመረ ብዙ ሺ አመታት ተቆጥረዋል- ይቆጠራሉም! ትንሳኤ ቆሞ ወደ ዘላለሙ ታዛ እንክንጓዝ ድረስ!

በስሌታዊ አስተሳሰብ አምናለሁ ባይ የሆነው የዘመኑ ሰው ይህን መሰል ስነግጥማዊና ስነ ፅሁፍዊ መርታትን የተጎናፀፈ ልዩ መንፈሳዊ ድርሣን የመቀበል አቅሙ የመነመነ ይመስላል ስለምን ቢባል በምንኖርበት ዘመን የምክንያታዊነት፣ ሳይንስ፣ ብሎም Logic (ስነ-አመክንዮ) ወይም ተገቢ አስተሳሰብ የሚሉት፣ ግንዛቤ ቅድሚያ ይሰጠዋልና ነው፡፡ ባንፃሩ ይህ እፁብ ድንቅ መፅሀፍ ከፈጣሪ የተወረደ መሆኑን የማይቀበሉ ሞልተዋል፡፡ ማንኛውም ሀይማኖታዊ ክታብ የተወረደ ለመሆኑ ማረጋገጥ ካሻ በውስጡ ያዘለው ምክንያታዊነት፣ ተገቢ አስተሳሰብ ሊመረመር ይገባዋል! በጠራ ልቦና፣ በሚዛናዊነት፣ ከራስ ከመነጨ ፍትሃዊነት እውነቱን ከቃኘነው ቁርዓን ይህንን መስፈርት እንደሚያሟላ ጥርጥር - የለውም!

በዝነኛው ሳይንቲስትና የኖበል ተሸላሚ የሆነው አልበርት አንስታይን አገላለፅ "ሳይንስ ያለ ሀይማኖት መሠረት አልባ ነው፡፡ ሀይማኖት ያለ ያለሳይንስ ደግሞ እውር ነው፡፡" ስለዚህ እውነታውን ይህ የአለም እውቁ ሰው ካበሰረ እንደምን? የራሳችንን ህሊና ጠይቀን መመራመር ይሳነናል? ከ1400 ዓመት በፊት የተወረደው

ቁርዓን በሳይንሳዊ እውነታ የታጀበ ለመሆኑ አሌ – የማይባል ሆኖ፤ ምጥቀታዊ ዘገባው እንደ ማለዳ ፀሀይ ፍንትው ያለ ነው! ለመሆኑ የማለዳ ፀሀይን ባይን – በብሌኑ ማየት የሚሳነው አለን?

ለማጠቃለል ቁርዓን በውስጡም ከ 6000 ሺ በላይ ምልክቶችን አዝሏል፡፡ ሳይንስም በሺዎች የሚቆጠሩ መረጃዎች ፍሬ ሃሣቦችን እጥቅም ላይ ለማዋል U-TURN ወይም ወደኋላ የተጠመዘዘ ይመስለናል፡፡ ወደ ቁርዓን!

እኛም ይህንን እውነታ ለማመላከት በእጅጉ እየጣርን ነው፡፡ የምርምር አድማሱን ለማስፋት የህሊና ግርዶሹን የገፈፈ እርሱነቱን፣ ምንነቱን፣ ያሁንም የወደፊት እጣውን ብሎም የፈጣሪና የፍጥረታትን ሁናቴ በቁርዓን ውስጥ ያገኘዋል… ልብ ያለው ልብ ካለ! ኑ በቁርዓን ጥላ ሥር እንጠለል ሌላው ቀርቶ የስነ ፅሁፋዊ ይዘቱ ተወዳዳሪ አልባ መሆኑ 'እውነትን እውነት ያሰኘዋል' የእውነቶች ሁሉ እውነት ደግሞ ህያዊ አምላክ በመሆኑ፤ ቁርዓን በገቢር ወደ ህያዊ አምላክ እንመራ ዘንድ የወረደ የመጨረሻ መልዕክት ነው! አይደለም ብሎ በፅናት የሚከራከር ካለ ያንን ከላይ የጠቀስነውን ቁርዓናዊ የግጥሚያ ጥሪ ወይም አል-በቀራህ ቁጥር 24-25 በዋቢነት እንሰጠዋለን!